# የሽብር አብዮት ወጣ ፤ የሰላም አብዬት ግባ ! ! !

*ፍርድያወቃል ጥበቡ*

ሰሞኑን የተለያዩ የማናኛ አውታሮችን በቅርብ ለምንከታተል ወገኖች ሁሉ የሁለት ኃይላት ድምጽና ፍጥጫ ጎልቶ የሚስማበትን አወድ በመንግሥት ሚዲያዎችና በግል ፕሬሶች እንሰማለን፣ እናነባለንም፡፡ ፍጥጫውም በሁለት ተቃራኒ አሚካከቶች ዙሪያ የሚያጠነጥን ሲሆን፤ ይህም በአንድ በኩል በፀረ-ሽብር ኃይሎችና በሌላኛው ጫፍ ላይ ደግሞ በማወቅም ይሁን ባለማወቅ በሽብርተኛ ዓላማ አቀንቃኞች መካከል ያለ የሃሳብና የአሚካከት ልዩነት በግልጽ የተንጸባረቀበት መሆኑን ማንዘብ አያዳግተንም፡፡ ለጊዜው በሁለቱም ወገኖች እየቀረቡ ያሉትን አንዳንዶች ትክክለኛና ሌሎች ደግሞ ትክክለኛ ያልሆኑ ዘገባዎችንና ትንታኔዎችን ለጊዜው እንለፋቸውና በሽብርተኝነትና የሱ ተቃራኒ በሆነው ሠላም ላይ ወይም በሽብርተኝነትና ልማታዊነት ላይ፣ አንዳንዴ እንደሚባለው ከአለም አቀፍ አጠቃላይ ልምድ አንፃር አንዳንድ ነጥቦችን እያነሳን በተጨባጭ እንወያይ ዘንድ የዚህ ጽሁፍ ዓላማ ነው፡፡ ይሁን እንጂ፣ የየራሳቸው የሆኑ ትርጓሜዎችንና አላማዎችን በውስጣቸው የያዙ ሁለቱን ጽንሰ ሃሳቦች እንሚከታለን እንበል እንጂ፣ ሠላምና ልማት የሚሉት በተወሰነ ደረጃ በብዙሃን አንባቢያን ዘንድ ግልፅ በመሆናቸው በአብዛኛው ትኩረታችን በአገራችን "ሽብር" እና "ሽብርተኝንት" በሚሉት ሁለት ወቅታዊ የመወያያ ነጥቦች ላይ በዋናነት የሚያተኩር ይሆናል፡፡ ጽሁፉ ከዚህም ጋር በሠላምና ልማት ላይ የሚያሳርፉትን ጥላም በስሱ ይዳስሳል፡፡ ይህ ከሆነ ዘንዳም "ሽብር" ከሚለው ጽንሰ ሃሳብ መጀመር ፈቀድሁ፡፡

በቅድሚያ "ሽብር" / terror / ወይም "ሽብርተኝነት" (terrorism) የሚለውን እንመልከት፡፡ ቃሉን በተማለከተ እስካሁን ድረስ ቁርጥ ያለ፤በሁሉም ወገኖች ዘንድ የጋራ ተቀበይነትን ያገኘ ወጥ ትርጎሜ /ብያኔ አልተገኘለትም ማለት ይቻላል፡፡ ሊኖረውም አይችልም፤አለያም አይገርምም ባይ ነኝ፡፡ ምክንያቱም የሽብር አራማጆችና ደጋፊዎች ቢያንስ ከሌሎች ተለይተው ለራሳቸው የሚሰጡት ቦታና በዚህም ለድርጊታቸው የሚሰጡት የራሳቸው ብያኔ ስላላቸው ከትርጓሜው ይልቅ ከሚያስከትለው ውጤት ጋር ተያይዞ በህብረተሰቡ ዘንድ የጋራ ተቀባይነትን ያገኘውና /ሰብአዊነቱ ቢጎድላቸውምና ኃላፊነት ባይሰማቸውም፤ከድርጊቱ ፈጻሚዎች ወገንም ቢሆን ቢያንስ ቢያንስ የሽብርተኝነትን ውጤትና አደገኛነት በሚታዘብ ደረጃ እንኳ ቢሆን/ የሽብርና ሽብርተኝነት እኩይ ዓላማና የሚያደርሰው ሰብአዊና ቁሳዊ ወድመት፤ ጥፋት፤የህዝቦች ሰቆቃና ማህበራዊ ቀውስ የከፋ መሆኑ ላይ ሁሉንም ወገኖች የሚያግባባ ይመስለኛል፡፡ ይህም አጠቃላይ ሰላም ወዳዱ የአለም አቀፍ ማህበረሰብ ሽብርና ሽብርተኝነትን በአንድ ድምፅ እንዲያወግዘው ግድ ብሏል፡፡ በመሆኑም በርካታ በጉዳዩ ላይ

የተደረጉ የተለያዩ ምሁራን ጥናቶችን ስንሚምር የየጥናቶቹ ማጠቃለያ፣ ሽብርተኝነት ኢ-ሰብአዊ ተግባር፣ ፀረ ሰላም እንቅስቃሴ፣ ፀረ-ልማት ዓላማን ያነገበ፣ የአፍራሽነት ተልዕኮን በግልፅ የሰነቀ…. ወዘተ ተግባር ሆኖ ነው የምናገኘው፡፡ በተለይ በዚሁ በሽብርተኝነት ዙሪያ ሰፋ ያለ ጥናት ያቀረቡት ተመራማሪዎች በየማጠቃለያቸው ላይ ከላይ ያልነውን ይበልጥ በሚያጠናክር መልኩ ይገልፁታል፡፡

ስለሽብርና ሽብርተኝነት አመጣጥ ብዙ የተባለ ቢሆንም ብዙዎቹን ትተን አንዱን፣ የ I.. Blishchenko and N. Zhdanovnን "Terrorism and International Law" (1984) በምሳሌነት እንወሰድ፡፡ ይህ መፅሐፍ ሽብርተኝነት በ16ኛ ክፍለ ዘመን መጨረሻና በ17ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ጀምሮ የዓለም መነናኛ ብዙሃን ጉዳዩን ማዘገብ እንጀመሩ ይገልፅና አጀማመሩንም ከአይሮፕላን ጠለፋና ጠላፊዎች ጋር የተያያዘ መሆኑን ገና ከመግቢያው ይገልፃል፡፡ ጉዳዩን የበለጠ ያብራራዋልና መጽሐፉን ማንበብ ጠቃሚ ነው እያልን ለጊዜው ወደ ጉዳያችን እንለፍ፡፡

በተቀረው ዓለም ሽብርተኞችና ተግባራቸው በአጠቃላይ ቢወገዝም በድርጊቱ ተዋንያን በኩል ለራስ የተሰጠ ፣ ወይም ራሳቸውን የሾሙበት የታሪክ አጋጣሚ እንደነበርና አሁንም በስፋት እንዳለ እንረዳለን፡፡ ይህም ራስን የመሾምና ተቀባይነትን ለማግኘት የሚደረግ ብርቱና ሰፊ ጥረት ራሳቸው፣ በራሳቸው፣ ለራሳቸው የሰጡት "የነፃነት ታጋይ" /Freedom fighter/ ይሉት ስያሜ አንዱ ማለጫ ነው፡፡ ተግባራቸውንም "አብዮት" /revolution/ ማለታቸው በተጨማሪ ማስረጃነት ሊወሰድ ይችላል፡፡ ምንም ይበሉ ምን፤ ራሳቸውን ማንም ይበሉት ማን ሽብርተኝነት ከአሸባነሪቱና አመፅኝነቱ ወጪ ሌላ ስያሜ ሊኖረውም ሆነ ሊያገኝ እንዳልቻለና "Terrorism is exactly violence" ከሚል የጥናት ውጤት መደምደሚያ ሊያመልጥ አለመቻሉን መረዳት አያዳግትም፡፡ ይህን ሃሳብ ይበልጥ ለማስረገጥ ከተፈለገ League of Nations Convention በ1937፣ United Nations Office on Drugs and Crime 1963፣ The Arab Convention for The Suppression of Terrorism 1998፣ Christian Science Monitor: Perspective on Terrorism እና የመሳሰሉ ሰነዶችን ማገላበጥ ጠቃሚ ይሆናል፡፡

በእነዚህ ሰነዶች ወስጥ በተለይም በአሜሪካ የሰብአዊ መብትና የህግ ተቋማትና ተመራማሪዎች ዘንድ በርካታ ቀጥተኛ (direct) እና ቀጥተኛ ያለሆኑ (proxy) የሽብርና ሽብርተኝነት አይነቶች ተለይተው የተመለከቱ ሲሆን፤ ከነዚህም መካከል አንዱ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ በመንግስታት የሚደረግ የሽብርተኝነት ተግባር ነው፤ ለዚህም የጀርመኑ ናዚ በገላጭ ምሳሌነት በአለም አቀፍ ደረጃ ይጠቀሳል፡፡ በተዘዋዋሪ አሸባሪነት ደግሞ በአንዳንዶች ዘንድ ኢራን ሂዝቦላን በመርዳትና

በማስታጠቂ ትጠቀሳለች፡፡ የግል አሜካከትን፤በአሣዛኝም ፖለቲካዊ እምነትንና ፍልስፍናን ወይም ርዕዮትን ብቻ ማስረት በሚድረግ ሆኖም ግን በምክንያት ያልተደገፈ አላማቸውን ለማስካት ከሚንቀሳቀሱ የሽብር ድርጅቶች መካከል ደግሞ አልቃኢዳና ተከታዮቹ ይጠቀሳሉ፡፡ እነዚህ አብዛኛው የአለም ህብረተሰብ የተስማማባቸው ከመሆናቸው አንፃር እዚህ ነጥብ ላይ ጠቅሰናቸው እንጂ ሌሎች በርካታ ማሳል ድርጅቶችም እንዳሉ ይታወቃል፡፡

ቀደም ሲል ለመጥቀስ እንደተሞከረው፣ እስካሁን በሀገር፣ አህጉርና አለም አቀፍ ደረጃ በሽብርና ሽብርተኝነት ዙሪያ እጅግ ብዙ በርካታ ምርምሮችና ጥናቶች ተከናውነዋል፤ የአለም ሚዲያዎች በጋራ መክረዋል፤ ህዝቦች ብዙ ተወያይተውበታል፡፡ እስካሁን ሽብርና ሽብርተኞችን ለሚደንና ለማጥፋት በርካታ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ወጥተው እየተሰራባቸው ይገኛል፡፡ ይህ የቆመ ጉዳይ ሳይሆን ጥናቶቹም ሆኑ ምክክሮቹና ወይይቶቹ እንደቀጠሉ ናቸው፡፡ ለጊዜው ግን በአንድ መሠረታዊ ጉዳይ ላይ ብዙዎቹ በማስማማት በዚሁ ዙሪያ ሃሳባቸውን በማጠንጠን ላይ ናቸው፡፡ እነዚህ የተለያዩ ነገር ግን አንድ አላማ ያላቸውን ፀረ-ሽብርተኝነት አቋሞች በማስተባበር ከሽብርተኝነት የፀዳች አለምን እንዴት መፍጠር ይቻላል?” የሚለው አቢይና ማዕከላዊ ነጥብ መሆኑ ላይም ብዙዎች ይስማማሉ፡፡ ይህም “ሽብርተኞችን ከነተግባራቸው ማጥፋት” በሚለው አጠቃላይ ሀሳብ ላይ ሁሉም ሰላማዊና ፀረ-ሽብር ወገኖች የጋራ መግባባት ላይ እንዲደርሱ የሽብርተኞች እኩይ ተግባር አስገድዷቸዋል፡፡ ሽብርተኝነት ካለው አለም አቀፋዊ ገጽታው አኳያም በሚችሉት አቅም ሁሉ እያደረጉ ያሉትም ይህንኑ ይመስላል፡፡

ወደ አንድ ቅርብ ጊዜ የሽብር ተግባር እንምጣና በሸልትላንድ ደሴቶች ወስጥ የተከሰተ ተግባርን በምሳሌነት እንጥቀስ፡፡ ጉዳዩ ጄክ ደቪስ በተባለ የ18 ዓመት ወጣት የተከናወነ የሽብር ተግባር ነው፡፡ የዚህ ወጣት ተግባር የበርካታ ሀገራትን የደህንነት፤ የፖሊስ ተቋማትንና ባለስልጣናትን፣ ግራ ሲያጋባ የቆየና በሚጨረሻም በቁጥጥር ስር የዋለ የሽብርተኝነት /Cybercrime/ Cyberterrorism/ ተግባር ነው፡፡ ድርጊቱም የድረ-ገፅ ተጠቃሚዎችን /Internet society /ነፃነትና መብት በሚጋፋ ሜልኩ የተከናወነ ሕገወጥ ተግባር ነበር፡፡ ወጣቱ የሰዎችን የፊት ገፅታና ሜልካም ስብዕና በማበላሸት /defacing/ እና በድረ-ገጾች አማካይነት የሚከናወኑ አበይት ተግባራትን በማወክ /disabling / በፈጸመው ድርጊት ምክንያት ድርጊቱ በራሱ እንደ አንድ የሽብርተኝነት እንቅስቃሴ በመወሰዱ ጉዳዩ ወደ ፍ/ቤት ተመርቶ የፍርድ ወሳኔ ተሰጥቶታል፡፡ በፍርድ ቤቱ ወሳኔ ማስረትም ማፍቸውም ለእስረኞች የተሰጡ መብቶች ተነፍገውት የዕድሜ ልክ እስራት “Real- life jail“ ተፈርዶበት ዘብጥያ ወርዷል፡፡ ዝርዝሩን ያስነበበን The Economist (August 6th 2011) መፅሔት እትም ነው፡፡ እዚህ ላይ ይህን የ18 ዓመት “ልጅ”

ታሪክ መጥቀስ ያስፈለገበት አቢይ ጉዳይ በሽብርና ሽብርተኝነት ላይ ምንም አይነት ህርራሄ ያለመኖሩን ለማየትና ብሎም ለሽብርተኝነት የሚሰጠው ትርጉም በተወሰነ ደረጃም ቢሆን እንደየሃገራቱ ሁኔታ ልዩነቶች የሚስተዋሉበት ስለሚሆኑ ለማጠቆም ነው፡፡ በሌላም በኩል የሽብርተኝነት ተግባር በተለያዩ /በዕድሜም ሆነ በሌሎች/ ጉዳዮችና ሁኔታዎች፣ ለሽፈንና ሊታለፍ እንደሚይቻል ነው፡፡

የሽብርተኝነት አይነቶችን በተመለከተ በርካቶች ብዙ ያሉ ሲሆን፤ ዝርዝራቸውም የዚያኑ ያህል ብዙ ነው፡፡ የአሜሪካው Law Enforcement Assistant Administration ያቋቋመው-ግብረ ኃይል (National Advisory Committee on Criminal Justice Standards and Goals) በሽብርተኝነት ላይ ባደረገው አምስት ቅጾች ያሉት ሰፊ ጥናት በአንደኛው "Disorders and Terrorism" በሚለው ቅጽ ወስጥ ስደስት ዋና ዋና የሽብርተኝነት አይነቶችን ከነብያኔያቸው ጭምር ለይቶ አስቀምጧል፣ ፡፡ ከነዚህ ወስጥ እንደኛው "ሁከት መፍጠር" /Civil disorder/ ሲሆን አቢይ አላማውም "የተደራጀ ሽብርተኝነት፣ በህብረተሰቡ ሰላም፣ ደህንነት፣ እና ህብረተቡ በሰላምና በተረጋጋ መንፈስ እያካሄደ ባለው ተግባር ላይ ጫሊቃ በመግባት ማወክ" (A form of Collective Violence interfering with the peace, security, and normal functioning of the community.) የሚለው ዋናው ሰነድ ነው፡፡

ለመሆኑ የሽብርተኝነት ዋና ዋና ምንጮች ምንድናቸው? ለዚህ ጥያቄ በርካቶች የተለያዩ ምክንያቶችን ዘርዝረዋል፡፡ ለምሳሌ ካርተን ቦክስቴቴ የተባሉ ተመራማሪ ሽብርተኝነትን ከአሸባሪዎች ስለልቦና አንፃር የፈተሹ የሽብርተኝነት ዋና ዋና ምክንያቶች ጭንቀት /ያጠቱን እንደገና ለማግኘት የሚደረግ ከንቱ ጥረት/፣ ግለኝነት፣ ርካሽ ዕወቅናና የሚዲያ ሽፋን ፍለጋ ... ወዘተ ናቸው ሲሉ፤ ሌናርት ጆበርግ በ Risk Management: An International Journal (2005) ወስጥ በተካተተ "The Perceived Risk of Terrorism" ጥናታዊ ፅሁፋቸው፣ ከላይ ከጠቀስነው ጥናት ጋር በተደጋገፈ መልኩ የሽብርተኝነት ዋና ዋና ምንጮች ካሏቸው በርካታ ነጥቦች መካከል ጭንቀት፣ ራስወዳድነት፣ የተዛባ መረጃ ባለቤት መሆንና በተዛባ መረጃ ላይ ተመስርቶ መንቀሳቀስ፣ ገብጋባነት፣ ተጠራጣሪነት ፣..... ይገኙበታል፡፡ በጆበርግ ጥናት መሰረት ሽብርተኝነት በቅድሚያ ሴቶችን፣ ሕፃናትንና አረጋወያንን ኢላማ ሚድረጉ ሌላው የሽብርተኝነት አስከፊ ገፅታው ነው፡፡ ወደ አፍሪካ ስንመጣም የሮበርት አይ ሮትበርግን "Battling Terrorism in the Horn Of Africa" (2005) ጥናት የምናገኝ ሲሆን የላይኛዎቹን ሰበቦች ጨምሮ ሌሎች ዋና ዋና የሚሏቸውን ጉዳዮች ከአፍሪካ ቀንድ አንፃር ይተነትናል፡፡ አላማቸው ምንም ይሁን ምን ምክንያታዊ ነን ይበሉም አይበሉ፤ ከላይ በገለፅናቸውም ሆነ ሌሎች በርካታ ጥናታዊ ፅሁፎች ማጠቃለያዎች ላይ

በመደምደምያነት የቀረበወና የተሰሚበት ሀሳብ “ሽብርተኝነትን ምንም አይነት ዓላማም ሆነ ርዕዮተ አለማዊ ጣጦዎች ከጥፋተኝነቱ፣ ኢ–ሰብአዊነቱ፣ ፀረ–ልማትነቱ … ወዘተ ሊታደጉት እንደማይችሉና ከምድረ ገፅ መጥፋት ያለበት እኩይ ድርጊት ከመሆኑ ወጪ የነፃነት ታጋይነቱን ሊያረጋግጡለትና ከፀረ–ዴሞክራሲያዊ አቋሙ ፈቀቅ አድርገው ሲያሸልሙት አይችሉም፡፡” የሚለው ሀሳብ ጠንካራ አቋም ሆኖ እናገኘዋለን፡፡

ባጠቃላይ፣ ስለሽብርና ሽብርተኝነት ከላይ በጥቂቱ ብለናል፡፡ በአዲስ አመት መግቢያ የሚገረወን የሃገራችንን ትወፊታዊ ስነቃል አገላለፅ ተጠቅመን በርዕሳችን ሽብርተኝነትን አወግዘን ሠላምን ነይ ግቢ ብለናል፡፡

ከላይ በርዕሰ ጉዳያችን ዙሪያ ሽብርና ሽብርተኝነት “የሁሉም ነገር ፀር” በሚባል ደረጃ ማለፁንና በአለም ህብረተሰብ ዘንድም ፍፁም የተወገዘ መሆኑን በማጡ ለመጠቆም የቻልን ይመስለኛል፡፡ በመሆኑም ሁላችንም ከሰላም ወዳዱ የአለም ህብረተሰብ ጎን በመቆም ሽብርተኝነትን ሟጋለጥና ማታገል ግድ ይለናል፡፡ የሽብርተኝነት ስጋት አለም አቀፋዊ ገጽታ ያለው ከመሆኑ አንጻርና በተለይም አደጋው በአጋጣሚ ቢከሰት የሚያስከትለው ጉዳት በሃገራችን አባባል "ነግ በኔ" ነወና ቢያንስ ሥጋቱ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ የሁሉንም ቤት የሚያንኳኳና ህልወናችንን ለከፋ አደጋ የሚያጋልጥ መሆኑን ተገንዝበን፤ የጸረ ሽብር ጎራን ይበልጥ ማጠናከርና መደገፍ ይገባናል፡፡ እናማ ዛሬም በአዲሱ አመት መጀመሪያ ላይ ሆነን ደግመን ደጋግመን አሁንኑ "ሽብር ይወጣ፤ ሰላም ይግባ " እንላለን!!!